በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ወርሃዊ የአየር ጠባይ

# ግምገማና ትንበያ መጽሔት

## ከጁላይ 1-31 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም

## ከኦገስት 1-31/2024 የሚኖረው ወርሃዊ የአየር ጠባይ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ


ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........ - 1 -

ምስል 1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ72 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች ........ - 2 -

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 4 -

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ........ - 4 -

ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 4 -

ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ ........ - 4 -

ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 5 -

ካርታ 13 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 5 -

ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 6 -

ካርታ 14 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 6 -

........ - 6 -

ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ ........ - 7 -

ካርታ 15 እ.ኤ.አ ከኦገስት1-31/2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር ........ - 7 -

ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 8 -

ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 8 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ


ባለፈው የጁላይ የመጀመሪያው እና ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በጁላይ የሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ይበልጥ ተጠናክረው የተስተዋለ ሲሆንና፤ በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተስተዉሏል፡፡

በአጠቃላይ በጁላይ ወር የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ማለትም የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ተደጋጋሚነት ያለው ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ40 ሚ.ሜ. በላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል፤ በአዲስ አበባ ቦሌ 44.0፤ በባህርዳር 67.8፤ በቢሾፍቱ 42.5 እና 41.5፤ በጎሬ 47.7፤ በጅማ 59.6፤ በአዲግራት 43.7፤ በአለም ከተማ 43.0፤ በአምባ ማሪያም 42.4፤ በአርሲ ሮቤ 74.2፤ በአይራ 46.8፣ 58.6 እና 53.2፤ በአማን 47.4፣ 58.8፤ በአምደወርቅ 42.5፤ በአንገር ጉትን 48.4፤ በአዴት 69.4፤ በአዋሽ አርባ 60.0፣ 50.0፤ በአፅቢ 112.0፤ በቡለን 60.4 እና 100.2፤ በቡሌ ሆራ 40.0፤ በቻግኒ 42.1፤ በጨፋ 44.2፤ በጭራ 55.5 እና 64.9፤ በዳሊፋጊ 117.3፤ በዳንግላ 72.0፣ 43.3፣ 47.2፤ በደባርቅ 44.0፤ በደብረ ብረሃን 43.6 እና 47.8፤ በእንዋሪ 118.2፤ በፉኚዶ 42.5፤ በጋምቤላ 46.2 እና 76.6፤ በወሊሶ 72.0፤ በጊዳ አያና 46.1፣ 67.3 እና 78.3፤ በሀረር 40.0 እና 53.0፤ በካቺሴ 56.6፤ በላሬ 78.0፤ በላይበር 54.7፤ በማጀቴ 40.9፤ በሜኢሶ 40.2፤ በሞጣ 50.8፤ በአዳማ 41.0 እና 63.8፤ በፅፅቃ 46.2፤ በወላይታ 44.1፤ በፓዌ 51.3 እና 51.6፤ በሰኮሩ 41.8፤ በስንቃጣ 42.0 በሻውራ 43.8፤ በሾላገበያ 40.7፤ በቴፒ 62.3፤ በያበሎ 68፤ በየትኖራ 41.7፤ በባቱ 44.4፤ በላንጌ 68.5 እና 56.0፤ በቁሉቢ 42.6 እና 46.6፤ በካራሚሌ 50.2፤ በጨለንቆ 90.4 እና 47.9፤ በግራዋ 49.5 እንዲሁም በጉብሬ 45.7 እና 43.2 በሚ.ሜ ይገኙበታል።



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በአጠቃላይ ባለፈው የጁላይ ወር በ118 የሀገሪቱ አከባቢዋች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ ስፈራዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 72-118.2 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ72 ሚ.ሜ በላይ ከበድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል አፅቢ፣ እንዋሪ፣ ቡለን፣ ጨለንቆ፣ ዳንግላ፣ ላሬ፣ ጋምቤላ፣ ጊዳ አያና፣ ዳሊፋጊ፣ ግዮን እና አርሲ ሮቤ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡




ምስል 1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ72 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


በጁላይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሆሮ ጉዱሮ ወለጋ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣

ማዕከላዊ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ሀሪ፣ ፈንቲ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ካማሺ፣ አሶሳ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል ኤረር፣ ሲቲ እና ፋፋን ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጳያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲኦ፣ ባስኬቶ፣ ደቡብ ኦሞ እና ደራሼ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች እንዲሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ ከ151-650 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ17-30 ቀናት ያህል ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከአፋር ክልል አውሲ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ቡርጂ፣ አሌ እና ኮንሶ ዞኖች ላይ ከ10-150 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-16 ቀናት ያህል ነበራቸው (ካርታ 9 እና 10)፡፡ እንዲሁም በጁላይ ወር በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ እስከ 30 ቀን የሚደርስ ድግግሞሽ እንደነበር እና በብዙ አከባቢዎች ላይም የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ከመደበኛ በላይ ነበራቸው(ካርታ 12) ፡፡


ባለፈው የጁላይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ አዊ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፋንቲ፣ አውሲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ እና ፋፋን ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ ማዣንግ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ ጠምባሮ፣ የየም ልዩ ዞን፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ደራሼ፣ አማሮ፣ ባስኬቶ፣ ጌዲኦ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳዉሮ፣ ኮንታ፣ ከፋ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና የምዕራብ ዞኖች እንዲሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 11)፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት




ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው የጁላይ ወር በአብዛኛው የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም የተገኘው ዝናብ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻልም አልፎ ከጁላይ ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ለመዝራትና አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ሚና ከመኖሩም በላይ ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ ቋሚ ተክሎች ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር በጎ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከፍተኛና ተከታታይነት የነበረው እርጥበት ለጎርፍ መከሰትና በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ያስከተለ ሲሆን ይህም ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በጎፋ፣ በደሴ፣ በሲቲ፣ በመአከላዊ ሲዳማ እና በጅማ እና በምዕራብ አርሲ ዞን ከነበረው የዝናብ መብዛትና ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የመሬት መንሸራተት የተከሰተ ሲሆን በሰብሎችና በእንስሳት ላይ ጉዳት አድርሷል (ካርታ 13)፡፡




ካርታ 13 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁላይ ወር በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ እና የኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ ወደ ግድቦች እና ወደ ተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከመጨመር እና የወንዞች ውኃ መጠንን ከማሳደግ አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው። በተጨማሪም በአንዳንድ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በተለይም የላይኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክል እንዲሁም በጥቂት የኦሞግቤ፣ የአዋሽ እና የዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም የሆነ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ጎርፍ፣ የወንዝ ዳርቻዎች እና የግድቦች የዉሃ ሙላት ክስተት በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ ተስተውሏል።
(ካርታ 14) ፡፡




ካርታ 14 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ

በመደበኛ ሁኔታ የኦገስት ወር ካለፉት የክረምት ወራት በተሻላ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን በመጠንም ሆነ በሥርጭት በከፍተኛ መጠን የሚያደርስበት ወር ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለተከታታይ ሰዓትና ቀናት የሚዘንብበትና በተጨማሪም በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የሚስተዋልበት ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለወንዞች ሙላትና ቅጽበታዊ ጎርፍ የሚከሰትበት ወር ነዉ፡፡

በመጪው የኦገስት ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በመነሳት በረዶ የቀላቀለ እና ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 15)፡፡




ካርታ 15 እ.ኤ.አ ከኦገስት1-31/2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ወር የሚኖረው እርጥበትና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች፤ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች የዉሃ ፍላጎትን ለማሟላት እና በአሁኑ ጊዜ እርጥበት በማግኘት ላይ ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት ከማሻሻል አንፃረ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሌላም በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በረባዳማና አካባቢዎች የውሃ በሰብል ላይ መተኛት፣ የመሬት አቀማመጡ ከፍታ ባላቸውና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ የመሬት መንሸራተትና በጎርፍ የመጠቃት እንዲሁም እርጥበት በሚበዛባቸው አካባቢዎች ደግሞ የሰብል በሽታ እና የአረም መስፋፋት ሊከሰት ይችላል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ሰብሎች በጎርፍ እንዳይጠቁ እና በማሳ ላይ ውሃ እንዳይተኛ የጎርፍ መቀልበሻዎችን  ማዘጋጀት፣ ከማሳ ውሰጥ ውሃን ማንጣፈፊያ ቦዮችን ማዘጋጀት እንዲሁም የፀረ-አረም እና የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱና የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈለጋል።

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የኦገስት ወር አብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን የሚያገኙ ሲሆን በተለይም በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው እና የመካከለኛው  የስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ወደ ግድቦች እና ወደ የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከመጨመር እና የወንዞች ውኃን ሙላት አቅም ከማጎልበት  አንጻር ጥሩ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡  በሌላ በኩል ሊኖር በሚችለው ከፍተኛ እርጥበት ጋር ተያይዞ የቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የወንዝ ዳርቻዎች በውኃ መጥለቅለቅ እና የግድቦች የውኃ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሊጨምሩና በመደበኛ ከሚደርሱበት የውኃ ከፍታ በላይ ሊደርሱና ከመጠን በላይ ሊሞሉ ስለሚችሉ የግድቦች የቅርብ ክትትል ስራን ማጠናከር ያስፈልጋል። በተጨማሪም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ በህይወት፣ በንብረትም ሆነ በመሰረተ ልማት ላይ ጉዳት እንዳያስከትል የጎርፍ ማፋሰሻዎች ማፅዳት እንዲሁም ግድቦች እና የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች ላይ የቅርብ ክትትል በማድረግ ስጋትን አስቀድሞ በመለየት ጉዳትን ለመቀነስ እና ብሎም ለማስቀረት የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et